EthioLion

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY
☎ 55 35 06, 55 17 89, 12 39 00 - Fax 251-1-55 31 55 - ✉ 882
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ - Addis Ababa, Ethiopia

ቁጥር
Ref. No. ...........

ቀን
Date ጥቅምት 5/2001 ዓ.ም

# መኢአድ የመከፋፈል አደጋ አልገጠመውም፡፡

## (ከመኢአድ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ)

ጥቅምት 4/2001 ዓ.ም በወጡ ሁለት የግል ጋዜጦች ላይ መላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እንደተከፋፈለ በተለይም በፓርቲው ፕሬዚዳንት በክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል እና የሰሜን ኢትዮጵያ ቀጣና ኃላፊ በሆኑት በምክትል ፕሬዚዳንቱ በአቶ አባይነህ ብርሃኑ መካከል መለያየት እንደተፈጠረ ተደርጐ ቀርቧል፡፡ ነገር ግን በመኢአድ ፓርቲ ውስጥ ምንም ዓይነት መከፋፈል ያልተፈጠረና ዜናዎቹ በሬ ወለደ በሚል አንባብያንን የማሳሳት መሠሪ ሥራ እንዳስተላለፉ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲረዳው እንፈልጋለን፡፡

ፓርቲያችን ከኢትዮጵያ ውጭ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ፣ በካናዳ፣ በአውሮፓ፣ በደቡብ አፍሪካና በአውስትራሊያ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች እንዳሉት የሚታወቅ ነው፡፡ እነዚህ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች በፓርቲ አባልነት ሳይሆን በድጋፍ ሰጭነት ፓርቲያችንን በሃሳብ፣ በገንዘብ፣ በቁሳቁስና በሞራል ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

ሰሞኑን በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ በሚገኙት በመኢአድ (በቀድሞ ቅንጅት) ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች መካከል ተፈጠረ የተባለው የሃሳብ ልዩነት አልፎ አልፎ የሚያጋጥምና ወደፊትም ሊያጋጥም የሚችል ነው፡፡ የድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ተወካዮች ጥቅምት 7/2001 ዓ.ም በዋሽንግተን ተገናኝተው ውይይት ያካሂዳሉ፡፡ በአሁን ወቅት አቶ አባይነህ ብርሃኑ እና ዶ/ር ታዬ ወልደሰማያት የፓርቲያችን አማካሪ ቦርድ ሊቀመንበር በድጋፍ ሰጭዎቻችን መካከል ያለውን መቀራረብ በማዳበር ለፓርቲያችን የተሻለ ድጋፍ የሚደረግበትን ሥራ እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡



Ethiopia will Prevail !

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የሚገኘውና ሰላማዊ ትግሉን የሚያካሂደውም ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ እሙን ነው፡፡ የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ፣ የላዕላይ ምክር ቤት አባላትና፤ የጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚገኙትና የፓርቲውንም ሥራ የሚያከናውኑት በአገራችን ውስጥ መሆኑም ግልፅ ነው፡፡ የማደራጀት፣ የመቀስቀስ ቢሮ የመክፈትና ሌሎችም ሥራዎች የሚሠሩት እዚሁ ነው፡፡ ሞት እስራት፣ ድብደባና ውክቢያ የሚደርሰውም እዚህ አገር ቤት ባለው ሕዝብ ላይ ነው፡፡ ሕዝቡም ሆነ አመራሩ ይህን ሁሉ ተቋቁሞ ኃይሉን በአንድነት አስተባብሮ እየሠራ በሚገኝበት ወቅት በድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ውስጥ በጥቂት ሰዎች መካከል የሃሳብ ልዩነት ስለተፈጠረ ብቻ መኢአድ ተከፋፈለ ብሎ መዘገብ ከእውነት የራቀ የፈጠራ ወሬ ነው፡፡ ድርጊቱ ከጋዜጣ ማሻሻጫነት ያለፈ ጥቅም የሌለው መሆኑን እየገለጽን በፓርቲያችን ላይ የተከፈተውን አፍራሽ ተልዕኮ አጥብቀን እንቃወማለን፡፡

የጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር የሚጠይቀውን እውነትን ለሕዝብ የማቅረብ ተግባርን ከውስጣቸው ያራቁ ጋዜጦች ማለትም አውራ አምባ ታይምስ ጋዜጣ ‹‹የኢንጅነሩና የአባይነህ ብርሃኑ ልዩነት የአሜሪካ ድጋፍ ሰጭ ኰሚቴን አናከሰ›› እና መሠናዘሪያ ጋዜጣ ‹‹መኢአድ የመከፋፈል አደጋ ላይ ነው ተባለ›› በሚሉ አሳሳች ርዕሶቻቸው የሌለና ያልተፈጠረ ጉዳይ ዘግበዋል፡፡ ጋዜጠኞች እንደ ባለሙያ የሚያቀርቡትን ዘገባ ከማሠራጨታቸው በፊት እውነት ስለመሆኑ እርግጠኞች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ዛሬ ውሸት ያሠራጩ ጋዜጦች ነገ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚታመኑ አይሆኑም፡፡ ልክ እንደበጉ እረኛ ተረት ደጋግሞ በመዋሸት በጐችን ለአውሬ እንዳስበላ ሁሉ ደጋግሞ የሚዋሽና ከእውነት የራቀ ተረታ ተረት የሚጽፍ ጋዜጣም በሕዝብ ዘንድ አድማጭ የሚያጣ ይሆናል፡፡

በተለይም የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ከዚህ በፊት የፓርቲያችን የአመራር አባላትን አስመልክቶ ለሕዝብ የተሳሳተ መረጃ ማሰራጨቱ ይታወሳል፡፡ ዛሬም ከአፈርኩ አይመልሰኝ እንዲሉ መረጃ በስልክ ስጡኝ ስል በአካል ካልሆነ እምቢ ተባልኩ፤ ወደ ጽ/ቤታቸው እንዳልገባ በጥበቃ ሠራተኞች ተከለከልኩ፤ ብደውል መልስ ተነፈኩ፤ ያሉት ፈጽሞ ሐሰት የሆነና የጋዜጠኝነትን ሥነ ምግባር ያጐደፈ ተግባር ስለሆነ ለወደፊቱ እንዲያርሙት እንመክራለን፡፡ እናም ጋዜጦቹ ቆም ብለው በማሰብ የጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር የሚጠይቀውን እውነት ለሕዝብ ሊያስነብቡ ይገባል እንላለን፡፡

የሚመኙትን የሚያወሩ፣ ኃላፊነት የጎደላቸው ጸሐፊዎች፣ የመኢአድን ጠንክሮ መቆምና በገጠርና በከተማ እያከናወነ ያለውን መጠነ ሰፊ የማደራጀት ሥራ

EthioLion.com

ያመጣቸው ሰዎች ጥረታችንን ለማኮላሸት የሚሸርቡት ሴራ በመሆኑ አባላትና ደጋፊዎች የተከፈተብንን አሉባልታ ከወሬ ያለፈ ፋይዳ የሌለው መሆኑን እንድታውቁትና የዚህን መግለጫችንን እውነትነት አጥብቃችሁ እንድትከታተሉትና እንድታረጋግጡት እናሳስባለን።

ድርጊቱ ሕዝቡ በተቃዋሚዎች ተስፋ እየቆረጠ ከትግሉ እንዲያፈገፍግ የማድረግና የገዥውን ፓርቲ በእጅ አዙር የማጠናከር ሥራ መሆኑን ሕዝባችን ልብ ሊል ይገባል እንላለን። በምርጫ 97 አካባቢና ከዚያም በፊት በተቃዋሚዎች ላይ ይዘምቱ የነበሩ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ዛሬ አንዳችም ሲሉ አይታዩም፤ ምክንያቱም እንደአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ የመሳሰሉት አዘጋጆች በግል ጋዜጣ ስም ተደራጅተው የእነሱን የቀድሞ ተግባር ያከናውናሉና።

በአገር ውስጥና በውጭ አገር ያላችሁ የፓርቲያችን አባላትና ደጋፊዎች በፓርቲያችን ላይ የደረሰ ምንም ዓይነት መናጋት የሌለ መሆኑን ተገንዝባችሁ እንደምን ጊዜውም ትግሉን እንድታጠናክሩ እናሳስባለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

ጥቅምት 5/2001 ዓ.ም

EthioLion.Com